# የዜጎች መድረክ

ኢዜማ

ቅፅ 1 ቁጥር 15 ጥቅምት 13 ቀን 2012 ዓ.ም

በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ


# ሴቶች እና ፖለቲካ



# ሥርዓት አልበኝነት ለራስ ጠላት መሆን ነው !

በዘመናዊው የኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ሕዝብ በተለይም ወጣቱ በኃይል የተጫኑበትን አምባገነን ሥርዓቶች ለመጣል የተለያዩ ዓይነት የትግል ስልቶች ተጠቅሟል፡፡ ግለሰቦችም ይሁኑ ቡድኖች ከእውነተኛ የሕዝብ ፍላጎት እና ምርጫ ውጪ የመንግሥት ሥልጣንን በመያዝ ፍትህን ሲያጎድሉና ሕዝብን ሲበድሉ፣ ለድርድርና ለሰላማዊ የፖለቲካ ውድድር ያሉትን መንገዶች ሁሉ ሲዘጉ፣ ልክኛ የሆነ የመንግሥትነት ሥርዓት አጥተዋልና ያለ ስርዓት በሆነ የሕዝብ ትግል ከሥልጣናቸው እንዲባረሩ ወይንም አካሄዳቸውን እንዲያስተካክሉ ይገደዳሉ፡፡

ይሁን እንጂ ለእንዲህ ያለ ፍትሃዊ ለውጥ የተደረጉ ሁለገብ ትግሎች እንደ ትክክለኛ የፓለቲካ ትግል ባህልና መሣሪያ ተወስደው የግለሰቦችን ወይንም የቡድኖችን ጥቅም በሌሎች ላይ በግድ ለመጫን የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ሥርዓት አልበኝነትን ይፈጥራሉ፡፡ በአሁኑ ግዜ በሀገራችን የምናየው ይኸንን ነው፡፡

የሕዝብ እውነተኛ የሥልጣን ባለቤት የመሆኛ የሽግግር መንገድ ላይ እንደመሆናችን፣ ጥቅማቸው የተነካ የፓለቲካ ነጋዴዎች፤ ሕዝብን በነፃነት ሳይሆን በፍርሃት ቆፈን ውስጥ ከቶ ሥልጣን ላይ ለመቆየት ወይንም ወደ ሥልጣን ለመምጣት የሚመኙ ግለሰቦችና ቡድኖች፤ የሠሩት ግፍና በደል ህሊናቸውን ያሳወራቸው ነገ ተጠያቂ የሚሆኑበት የተረጋጋ ሥርዓት እንዳይፈጠር የሚሹ ግለሰቦች፤ እንዲሁም ግርግር ለሌባ ይመቻል እንዲሉ የሀገርን እና የሕዝብን የተፈጠሮ ኃብቶች ለመዝረፍ፤ ዜጎች ለዘመናት የደከሙበትን ኃብት እና ንብረት በርካሽ ወይንም በጉልበት ለመንጠቅ ያሰፈሰፉ ኃይሎች ሥርዓት አልበኝነቱን እንደሚያደራጁ፣ እንደሚያበራታቱ እና እንደሚደግፉ አያጠራጥርም፡፡

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በሀገር ደረጃ እያለፍንበት ያለው የሽግግር ወቅት ኢትዮጵያ ውስጥ ተመስርቶ ማየት ወደምንፈልገው እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በሰከነ መንገድ መሄድ አለበት ብሎ ያምናል፡፡ ለዚህም አመራሩ፣ አባላቱ እና ደጋፊዎች የሚያደርጓቸው ንግግሮች እና እንቅስቃሴዎች በሙሉ ሁልጊዜ ሰላማዊ እና ለሀገር መረጋጋት አዎንታዊ ሚና የሚጫወቱ ናቸው፡፡

ሌሎች የፖለቲካ ኃይሎችም ሀገራዊ መረጋጋትን እና ወደ ዴሞክሲያዊ ሥርዓት የምናደርገውን የጋራ ጉዞ የሚያደናቅፉ ንግግሮች እና ተግባራት ከማድረግ እና ሌሎች እንዲያደርጉ ከማነሳሳት እንዲታቀቡ በአክብሮት እንጠይቃለን፡፡
በአንድ ሀገር ውስጥ ሕዝብ ለሥርዓት ተገዢ እንዲሆን የማድረግ ኃላፊነት የሁሉም ዜጎችና ተቋማት ቢሆንም በዋናነት ግን የሚመለከተው በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥትን ነው፡፡ መንግሥት ዜጎች ያለስጋት ሕይወታቸውን እንዲመሩ የማስቻል ግዴታ አለበት፡፡ ፍትህና ሥርዓትን ማስከበር የመንግሥት ተቀዳሚ ተግባር ነው፡፡ መንግሥት በሁሉም የሀገራችን ክፍል ውስጥ በሕግ ላይ ተመስርቶ የመወሰን፣ የመቆጣጠር፣ የመዳኘት እና የመቅጣት ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል፡፡ ይህ ሳይሆን ቀርቶ የመንግሥትን ተግባር ግለሰቦች ወይንም ቡደኖች ማስፈፀማቸውን የሚቀጥሉ ከሆነ ኪሳራው ለሁላችንም ይሆናል፡፡

# ኢዜማ ለሕግ ማሻሻያ ግብዓት በሚሆኑ ጥናታዊ ጽሑፎች ላይ ውይይት አደረገ

ጥቅምት 13 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)




የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ለሕግ ማሻሻያ ግብዓት በሚሆኑ በባለሙያዎች በተዘጋጁ የተለያዩ ጥናታዊ ጽሑፎች ላይ የአንድ ቀን ውይይት አካሄደ፡፡

ለኢዜማ ለፖሊሲ ግብዓት በሚሆኑ ጥናታዊ ጽሑፎች ላይ ውይይት ማድረግን ዓላማው አድርጎ የተዘጋጀው መድረክ ላይ 5 የሚሆኑ ጥናታዊጽሑፎች በባለሙያዎችና በምሁራኖች ቀርበዋል፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የህግ መምህር የሆኑት ስሜነህ ኪሮስ በኢትዮጵያ ውስጥ የወንጀል አስተዳደሩ ምን ይመስላል? መሠረታዊ ችግሮቹና መስተካከል ያለባቸው ጉዳዮች ምን ምን ናቸው? በሚል ርዕሰ ጉዳይ ጥናታዊ ጽሑፍ አቅርበዋል፡፡ በተመሳሳይም ኤፍሬም ማዴቦ ፌዴራሊዝም ምንድን ነው? በዓለም ላይ ምን ምን ዓይነት የፌዴራሊዝም ሥርዓቶች አሉ? የሚለውን ያቀረቡ ሲሆን የኢዜማ የህግ ጉዳዮች ኮሚቴ ሰብሳቢ የሺዋስ አድማሱ የራስን እድል በራስ መወሰን ላይ ያተኮረ ጽሑፍ አቅርበዋል፡፡

በቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፎች ላይ ባለሙያዎቹ ችግሮች ብለው ካነሷቸው በተጨማሪ መፍትሔዎቻቸውና አማራጭ ሃሳቦች የሚሏቸውን አቅርበዋል፡፡ በውይይቱ ላይ ከታዳሚዎች ለቀረቡ ጥያቄዎችም ምላሽ ተሰጥቷል፡፡

የኢዜማ መሪ ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር) እና የፓርቲው ሊቀመንበር የሺዋስ አሰፋን ጨምሮ የኢዜማ ብሔራዊ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት እና የአዲስ አበባ ምርጫ ወረዳ አመራሮች በውይይቱ ላይ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡

## አድራሻ

ስልክ
+251118592950

ኢሜይል
ethzema@gmail.com

ትዊተር
www.twitter.com/ethzema

ፌስቡክ
www.facebook.com/ethzema

የኢትዮጵያ ዜጎች
ለማኅበራዊ ፍትህ
(ኢዜማ)

ጥቅምት 13 ቀን 2012 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# ሴቶች እና ፖለቲካ

«ሴቶች ከሁሉም አይነት ጭቆና ካልተላቀቁ በቀር ነጻነት ሊሳካ አይችልም፡፡»
ኔልሰን ማንዴላ

ሁሉም ዜጎች ሕዝብን እና ሀገርን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ እንዲሳተፉ ማመቻቸት የዴሞክራሲ መሰረት ነው፡፡ በተመሳሳይ ወንዶችም ሴቶችም በሙሉ እና እኩል በፖለቲካ ውሳኔዎች ላይ ሲሳተፉ ሚዛናዊነት እና ፍትህ እንዲኖር ከማስቻሉም በላይ፤ በማኅበረሰቡ ውስጥ ዴሞክራሲያዊነት እንዲሰፍን ይረዳል፡፡

በዚህ አጭር ጽሑፍ ውስጥ በሀገራችን የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ምን ይመስል እንደነበር፣ አሁን ካለበት ሁኔታ ጋር እናስተያያለን፡፡ የሴቶች በአመራርነት መሳተፍ ጠቀሜታውንና አስፈላጊነቱን እናስረዳለን፡፡ በሀገራችን ሴቶች ወደፊት መጥተው በአመራር ሰጪነት ከወንዶች እኩል እንዳይሳተፉ መሰናከል የሆኑባቸውን ምክንያቶች እና ድክመቶች እናነሳለን፡፡ በመጨረሻም ኢትዮጵያውያን ሴቶችን በፖለቲካና በውሳኔ ሰጪነት ቦታዎች ላይ ተሳትፈው ሀገራችንን ሁላችንም የምንፈልግበት ቦታ ላይ በማድረስ ሂደት ውስጥ በእኩልነት አሻራቸውን እንዲያሳርፉ እንደማኅበረሰብ እንደሀገር ምን ማድረግ እንደሚገባን መፍትሔ ለመጠቆም እንሞክራለን፡፡

በጥንቱ የሀገራችን ወግ ልማድ ረገድ የፖለቲካ ተሳትፎና የኃላፊነት ሚና በተለይም አስተዳደር ነክ ጉዳዮች ለወንዶች ብቻ የተተወ ይመስላል። በአክሱም ገናና ከነበረችው ከንግሥተ ሳባ ወዲህ ከልጇ ከቀዳማዊ ምኒልክ ጀምሮ የሰሎሞናውያን ሥርወ መንግሥት ንግሥና በወንዶች በኩል እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡ በ12ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሥልጣን የያዘው የዛግዌ ሥርወ መንግሥትም ሴትን በንግሥትነት አላስቀመጠም። ከዛግዌ ዘመነ መንግሥት ፍጻሜ በኋላ በአፄ ይኩኖ አምላክ እንደገና ያንሰራራው ሰሎሞናዊ ሥርወ መንግሥትም ወራሾቹ ወንዶች እንዲሆኑ ክብረ ነገሥት ላይ በተደነገገው አሠራር እንዲተገበር አድርጓል።

ከዚያን ዘመን ሴት መሪዎች የአፄ በካፋ ሚስት የነበረችውና ለአስተዳደር አቅም ያልደረሰው ብላቴና ልጇ ሥልጣን ሞግዚትነት ሰበብ አድራጊ ፈጣሪ ሆና ብቅ ያለችው ገናናዋ እቴጌ ምንትዋብ ትጠቀሳለች፡፡ የአመራርነት ብቃት እየተወጣች በልጇ አቤቶ እያሱ ስም ያስተዳደረችው ብልሃተኛ ሴት በርካታ የሥልጣን ተቀናቃኞችን ከውስጥም ከውጭም ተጋፍጣለች፡፡

ሌላዋ ከኢማም አሕመድ ሞት በኋላ የተበታተነ ሠራዊቱን አስተባብራ በአዋጊነት ከፊት የመራችው ባቲ ድል ወንበራ፣ ወሎ ውስጥ ታዋቂ ሴት ባላባቶች የነበሩ ወርቂት እና መስታወት ከዘመናዊት ኢትዮጵያ ታሪክ በፊት በነበረው ዘመን ውስጥ ፍንጥቅ ያሉ ሴቶች መሪዎች ናቸው፡፡

በዘመናዊ የኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የወንድ የበላይነት በሕግና በባህል የነገሠበት ዘመን እቴጌ ጣይቱ የነበራት ተሳትፎ ቀላል አልነበረም፡፡ እቴጌ ጣይቱ የጦር መሪ፣ የጦርነት ዘዴ ቀያሽ ሴትም ነበረች፡፡ አፄ ምኒልክ የውጫሌን ውል ቀደው በጣልያን ላይ ጦርነት እንዲታወጅ ጠንካራ አቋም የወሰደች ነበረች፡፡ ኢትዮጵያውያን ሴቶች በአድዋ በተዋጊነትና በጦርነቱ የተጎዱትን ወታደሮች በማከም እንዲሳተፉ አድርጋለች፡፡

የአባቷን ዘውድ ጭና ንግስተ ነገሥታት ለመሆን የበቃችው እቴጌ ዘውዲቱም ተጠቃሽ ንግሰት ናት፡፡ አፄ ምኒልክ የልጅ ልጃቸውን ልጅ እያሱን አልጋ ወራሻቸው ማድረጋቸው ለሴቶች በዘመኑ የነበረውን አስተሳሰብ ቢያሳይም ከልጅ እያሱ ውድቀት በኋላ ዘውዲቱ እንድትነግሥ በመኳንንቶች ይሁንታ መገኘቱ አስገራሚ ነው።
የአፄ ኃይለስላሴን ዘውዳዊ ሥርዓት የደርግን ሥርዓት ለመጣል በተደረጉት ትግሎች ውስጥ በርካታ ሴቶች ተሳትፈዋል፡፡ ለምሳሌ ማርታ መብራሀቱ ዘውዳዊው ሥርዓቱን በመቃወም አይሮፕላን እስከመጥለፍ ከደረሱት ሴቶች አንዷ ነበረች፡፡ በወቅቱ በነበሩት ፓርቲዎችም ከተራ አባልነት እስከ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባልነትም የደረሱ ሴቶች ነበሩ፡፡ ሀገራችን ሞልቶ ከተረፋት የሺህ አመታት ታሪክ ውስጥ በጣት የሚቆጠሩ ሴቶች ብቻ ጎልተው ይጠቀሳሉ፡፡

በአሁኑ ወቅትም አብዛኞቹ የዓለም ሀገራት ፖለቲካ እና ውሳኔ ሰጪነት በአብዛኛው በወንዶች የተያዘ ነው፡፡ በአንዳንዶቹ ደግሞ ለወንዶች ብቻ የተፈቀደ ነው፡፡ በሀገራችንም፣ ምንም እንኳን በፆታ ተመጣጣኝ ካቢኔ ቢኖረንም በፌደራል ፓርላማም ሆነ በሌሎች ምክርቤቶች ያለው የሴቶች ቁጥር እጅግ አነስተኛ ነው፡፡

## የሴቶች በፖለቲካ መሳተፍ ጠቀሜታው ምንድነው?

የሴቶች ፖለቲካዊ ተሳትፎ ለምን አስፈለገ ለሚለው ጥያቄ እንደ ዋነኛ ምክንያት የሚያነሳው የፍትህ ጥያቄ ነው። ግማሹን ወይም ከዚያ በላይ የኅብረተሰቡን ክፍል የያዙት ሴቶች በራሳቸው መወከላቸው አስፈላጊ ነው። ዴሞክራሲ የውክልናም ጥያቄ ሆኖ ሳለ ሴቶች ከቁጥራቸው አንፃር ሳይወከሉ እና ድምፅ ሳይኖራቸው በራሳቸውም ሆነ በማኅበረሰባቸው ጉዳይ በበቂ ሁኔታ ተሳታፊ ሳይሆኑ ዴሞክራሲን ማሳካት የማይታሰብ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም ሴቶችን ያገለለ የፖለቲካ ሥርዓት ዴሞክራሲያዊነት ጥያቄ ውስጥ ይገባል።

የሴቶች በሕግ አውጪው በሕግ አስፈፃሚው እንዲሁም በሕግ ተርጓሚው አካላት ላይ በብዛት እና በተመጣጣኝ ሁኔታ ካልተወከሉ በማኅበረሰብ ውስጥ በዋነኛነት ቅድሚያ የምንሰጣቸው ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ግቦችን ለማረጋገጥም ሆነ ለማሳካት የሚረዱንን አሳታፊ፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት አሰራርን ማምጣት አይቻልም።

ሌላኛው ደግሞ ሴቶች የየእለት የሕይወት ልምድ በተለይም ከታሪካዊ ፆታዊ ኢ-ፍትሀዊነት ጋር ተያይዞ መስተካከል

ያለባቸው ሕግጋትንና አፈፃፀማቸውን ለሴቶች ከሴቶች በላይ የሚያውቅ ስለሌለ ነው። ይህም ለሴቶች የተሻለች ሀገርን በመሥራት ሂደት ውስጥ አስፈላጊ ግብዓቶችን ከሴቶች በላይ ለመረዳት ከባድ ነው፡፡ ለበርካታ ዓመታት ሴቶችንም ሆነ ማኅበረሰቡን የሚመለከቱ ውሳኔዎች በወንዶች ሲወሰኑ ነበር፡፡ ወንዶች መወሰን የለባቸውም ሳይሆን እስከመቼ ድረስ የሚለው ጥያቄ መጠየቅ አስፈላጊ ነው፡፡

የሴት የፖለቲካ ተወካዮች ከሴቶች መብት በተጨማሪ የሕፃናትም መብቶች

እነዚህ ዓለምአቀፍ ድንጋጌዎች ቢኖሩም ሴቶች በምርጫ የፖለቲካ ሥልጣን የማይዙበት ሁኔታ መድሏዊ በመሆኑ ሳይተገበር ቀርቷል፡፡ ይህንን ለማስወገድ የተባበሩት መንግሥታት እ.ኤ.አ. በ1952 የመጀመሪያውን የሴቶች የፖለቲካ መብቶች ኮንቬንሽን ሥራ ላይ አዋለ፡፡ ከዚያም እ.ኤ.አ. 1979 የወጣው በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ማናቸውም ዓይነት መድሎዎችን ለማስቀረት የተፈረመው ስምምነት የሴቶችን የፖለቲካ መብት ከሚያረጋግጥ ባለፈ መንግሥታት በተጨባጭ ሴቶች ተሳታፊ

ፖለቲካዊ ተሳትፎን ጨምሮ ከወንዶች ጋር እኩል መብት እንዳላቸው አረጋግጧል፡፡ በተጨማሪም በሕገ መንግሥቱ መሠረት ሴቶች የአወንታዊ የድጋፍ እርምጃዎች ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ የተደነገገ ሲሆን፣ እርምጃው የፖለቲካውን ዘርፍም እንደሚመለከት በሕገ መንግሥቱ ተደንግጓል፡፡

አዲሱ ተሻሽሎ የፀደቀው የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ስነምግባር አዋጅ የፆታ እኩልነት የሚያበረታቱ አንቀፆችን ይዟል። ለምሳሌ ለፖለቲካ ፓርቲዎች ከመንግስት የሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍን

> ‹‹በተለይ በኛ ባህል የሴት ስኬትን ከባሏ ገቢ፣ ወይም ለልጆቿ ጥሩ እናት ከመሆኗ አንፃር ብቻ ይለካል፡፡ ሴት በትምህርቷ ወይም በሥራዋ የምታስመዘግበው ስኬት ጥሩ ሚስት ወይም እናት ከመሆን አይወዳደርም፡፡››

እንዲከበሩ በተሻለ ይሠራሉ፡፡ ሴቶችና ሕፃናትን የሚጠቅሙ ሕግጋት እንዲቀረጹና እንዲፈጸሙ የበኩላቸውንም አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡ አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት የሴቶች በውሳኔ ሰጪነት የመሳተፍ ሁኔታ በጨመረ ቁጥር በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚታዩ ማኅበራዊ ችግሮችን (የጤና፣ የምግብ እና የትምህርት) ለመቅረፍ የሚያስችሉ ሁኔታዎች በበለጠ ይጠናከራሉ፡፡

የማኅበረሰቡ አካላት የሆኑ ክፍሎች በሀገር ኢኮኖሚያዊ ማኅበራዊ እና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ ካልተደረገ ዴሞክራሲያዊ ሂደቱ ጥያቄ ውስጥ ይገባል።

## የሴቶችን ተሳትፎ ዓለም አቀፍ እና ሀገር አቀፍ ህጎች እንዴት ያዩታል?

የሴቶች በፖለቲካ የውሳኔ ሰጭነት የመሳተፍ መብት በ1948ቱ የተባበሩት መንግሥታት ዓለምአቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ቃልኪዳን ዕውቅና አግኝቷል፡፡ የዚህ ቃልኪዳን አንቀጽ 2 እና 21 ሴቶች በጾታቸው ምክንያት መድሎ ሳይደረግባቸው የፖለቲካ መብቶቻቸውን እንዲጠቀሙ ደንግጓል፡ ፡ እ.ኤ.አ. በ1966 ዓ.ም የወጣው የፖለቲካና የሲቪል መብቶች ቃል ኪዳን የሴቶች በመንግሥትና የፖለቲካ ሕይወት ያለምንም መድልኦ የመሳተፍ መብታቸውን አጠናክሮ ይደነግጋል፡፡

የሚሆኑበትን አሠራር በመተግበር የሴቶችን እኩልነት እንዲያፋጥኑ ግዴታ ይጥላል፡፡ በአሁኑ ወቅት ሀገራችንም እነዚህን ስምምነቶች ፈርማለች፡፡

የአፍሪካ የሴቶች ፕሮቶኮል እ.ኤ.አ. በ2003 ሲወጣ ሴቶች በፖለቲካ እኩል ተሳትፎ እንዲኖራቸው አጽንኦት የሰጠ ሲሆን፣ አዎንታዊ የልዩ ድጋፍ እርምጃ (Affirmative action) የሴቶችን በፖለቲካ ተሳታፊነትና ውጤታማነት እንደሚያረጋግጥ በማመን ሀገሮች እንዲተገብሩት ደንግጓል፡፡ ሀገራችን ይህን ፕሮቶኮል ባታፀድቅም ብዙ የአፍሪካ ሀገሮች አፅድቀውታል፡፡

ሴቶች በፖለቲካ ውሳኔ አሰጣጥ ያላቸውን ተሳትፎ ለመጨመር ሀገራችን የተሳተፈችባቸው ጠቃሚ ውሳኔዎችና የልማት ማዕቀፎች አሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ የ1995ቱ የቤይጂንግ መግለጫና የድርጊት መርሃ ግብር እና በ2000 የወጣው የሚሊኒየሙ የልማት ግቦች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ለምሳሌ የሚሊኒየሙን የልማት ግቦች ስለፆታ እኩልነት ብንመለከት ሴቶች በሕግ አውጭ አካል (ፓርላማ) የሚይዙት ቁጥር ከተቀመጡት ሦስት ማሳያዎች አንዱ ነው፡፡

የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 35 ሴቶች ሕገ መንግሥቱ ባረጋገጣቸው መብቶችና ጥበቃዎች በመጠቀም ረገድ

በተመለከተ ፓርቲዎች የሚያቀርቧቸውን የሴት እጩ ተወዳዳሪዎች፣ የሴት አመራሮችና አባላት ብዛት እንደመስፈርት ያስቀምጣል። ይህ መስፈርት ፖለቲካ ፓርቲዎች ሴት እጩዎችን እንዲያቀርቡ የሚያደርግ ሳቢ እርምጃ ነው፡፡

## ታዲያ እነዚህ ማዕቀፎች እያሉን ሴቶች ወደፊት መጥተው እንዳይሳተፉ ምን ተግዳሮት ያጋጥማቸዋል?

ሴቶች ወደ ፖለቲካ ውሳኔ ሰጪነት እንዳይመጡ የሚያደርጓቸው ጉዳዮች ከሀገር ሀገር ይለያያሉ፡፡ ነገር ግን እንደአጠቃላይ ሁሉም የሚስማሙባቸው ምክንያቶች አሉ፡፡ የመጀመሪያው ማኅበራዊ ተፅዕኖ ነው።

ይህም በዋናነት ባህላዊና ኋላቀር አስተሳሰብን ይመለከታል። ሴቶችን ከአደባባይ ሥራ ይልቅ በጓዳ የሚገድብ ባህል ባለበት ሴቶች ከልጆች አስተዳደግ ውጭ ያላቸውን ወይም የሚኖራቸውን ሚና የሚቀበል አሠራር መገንባት አስቸጋሪ ነው፡፡ በተለይ በኛ ባህል የሴት ስኬትን ከባሏ ገቢ፣ ወይም ለልጆቿ ጥሩ እናት ከመሆኗ አንፃር ብቻ ይለካል፡፡ ሴት በትምህርቷ ወይም በሥራዋ የምታስመዘግበው ስኬት ጥሩ ሚስት ወይም እናት ከመሆን አይወዳደርም፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ በርካታ ሴት ህፃናት ከትምህርት ቤት ቀርተው ያለእድሜያቸው ይዳራሉ። በብዙ የኢትዮጵያ አካባቢዎች ሰዎች ሴትን የማስተማር፣ ውሳኔን የሚጠይቁ ኃላፊነቶችን የመስጠት ጥቅምን

አልተረዱም። ይህም ሌላው ምክንያት ነው፡፡ በርካታ ሴቶች ይደፈራሉ፣ ጠለፋም ይካሄድባቸዋል። ይህ የሴቶች ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃትም እንደምክንያት ሊጠቀስ ይችላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በማኅበረሰባችን ለሴት ልጅ ጠያቂነት እና ኀላ ብሎ መታየት አልተፈቀደም ፡፡ እንዲያውም ሴቶች ቅልስልስ፣ አንገት ደፊ እንዲሆኑ ይጠበቅባቸዋልና ፖለቲካው የሚጠይቀውን ሞጋችነት እና ሃሳብን በልበሙሉነት መግለፅ ሳያጎለብቱ ያድጋሉ፡፡ ይህ በተለያዩ አባባሎች ይገለፅ እንደነበረ ይታወሳል፡፡ ለምሳሌ፡- “ሴት ከማጀት ወንድ ከአደባባይ”፣ “ምን ሴት ብታውቅ በወንድ ያልቅ”፣ “ሴት ባሰበች በዓመቱ ወንድ ባሰበ በእለቱ”... እነዚህ አባባሎች ሴት ልጅ ፋይዳ እንደሌላት መታየቱ ብቻ ሳይሆን ከዚህ የተነሳ በቀደመው ጊዜ በኢኮኖሚም የእኔ የምትለው መሬት፣ የንብረት ባለቤትነት መብት እንዳይኖራት በሕግም ተደግፎ ተግባራዊ እየሆነ ነበር፡፡

በዚህ ረገድ ሃይማኖቶችም አስተዋፅኦ ያደርጋሉ። ምንም እንኳን የእምነት ጉዳይ ቢሆንም፣ ለማኅበረሰብ ባህል እና ልማድ ሃይማኖቶች ምንጭ ከመሆናቸው አንፃር በአብዛኛዎቹ በእምነት ቤቶች የወንዶች መሪነት ስለሚያመዝን ይህ ሴቶች በባህላቸውም አካባቢ ከመሪነት እንዲቆጠቡ ያደርጋቸዋል። ሌላው ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ ነው። ሴቶች ለዘመናት የሀገር ይቅርና የቤታቸውም ኢኮኖሚ እና ገንዘብ ነክ ጉዳዮች ላይ በወንዶች ጥገኝነት ስር መኖራቸው ውሳኔ ሰጪነታቸውን በመገደብ ትልቅ ሚና ተጫውቷል። ከቤት ውጪ ወጥተው ቢሰሩም ማኅበረሰቡ ውስጥ እና በቤታቸው ያለባቸው ኃላፊነት ሌሎች መሰል ኃላፊነቶችን እንዲወስዱ ጊዜ አይሰጣቸውም። በተጨማሪም ለእንደዚህ ያለው ፖለቲካዊ እና የአመራር ሁኔታ ላይ ተጋላጭነታቸው አነስተኛ በመሆኑ በቂ እውቀት እና በራስ መተማመንን ስለማያዳብሩ ወደፖለቲካው ዓለም አይመጡም።

ከነዚህ በተጨማሪ ሴቶች ፖለቲካን መቀላቀል ይሹ እንደሆን ሲጠየቁ መልሳቸው አሉታዊ ነው፡፡ ምክንያታቸውም ፖለቲካ ቆሻሻ ነው የሚል ነው፡፡ እርግጥ ነው እንደኛ ላለ ፖለቲካ ሲባል እስር፣ ግርፊያ እና ስደት ትርጓሜው ለሆነበት ሀገር ዜጎች ለመሳተፍ ወደኋላ ማለታቸው የሚያስገምታቸው ጉዳይ አይሆንም፡፡ ነገር ግን እንደ አሜሪካ ያሉ የጾታ እኩልነት የሚያስከብር ሕግ ያላቸው ሀገራት እንኳን እስካሁን የመሪነቱን ወንበር ለሴቶች አለቀቁም። በተቃራኒው ደግሞ ላይቤሪያ ከብዙ ዓመታት ጦርነትና ከምስቅልቅል የሕዝብ ኑሮ በኋላ ሰላም ለማስፈንና ሀገርን አንድ አድርገው ለመምራት የበቁ ሴት ፕሬዚዳንት መርጠው ነበር፡፡

ከላይ ከዘረዘርናቸው ችግሮች ባሻገር ፖለቲካ ፓርቲዎችም የማኅበረሰቡ ነፀብራቅ እንደመሆናቸው ሴቶችን በብዛት ሲያሳትፉና ወደአመራርነት ሲያመጡ አይታይም፡ ፡ ይህም በፖለቲካው ዓለም ትልቁ ተዋናይ የሆኑት ፖለቲካ ፓርቲዎች እንደመሆናቸው ሴቶችን ትኩረት አድርገው አለመሥራታቸው ሴቶች በርትተው ይህ የኔም ቦታ ነው ብለው እንዳይመጡ ከማድረጉም ባሻገር በውስጥ ያሉት ሴቶች ጠንካራ፣ ተፋላሚ፣ ጠያቂና ውሳኔ ሰጪ እንዳይሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡

## አሁን ወደ ዴሞክራሲ በምናደርገው ጉዞ ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ እንዲጠናከር እና በማኅበረሰባችን እኩልነት የሰፈነበት ሁሉም አካላት በእኩልነት የሚወከሉበት እንዲሆን ምን ማድረግ ይገባናል?

የሀገራችን ፖለቲካ በሃሳብ እና በምክንያት የሚመራ እንዲሆን ማድረግ የመንግሥትና የእያንዳንዱ ዜጋ ኃላፊነት ነው፡ ፡ ፖለቲካችን በአጠቃላይ ሲሻሻል እና ዜጎች ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ እና የመደራጀት መብቶቻቸው ሲከበሩላቸው ሴቶች እንዲሁም ወንዶች ወደፖለቲካው ዓለም ለመግባት የምን ይደርስብኝ ይሆን ፍርሃት አያድርባቸውም፡፡ ለሴቶች ተጨማሪ ፈተና የሆነባቸውን የማኅበረሰብ ኋላቀር ልማድ እና አስተሳሰብ እንዲሁም የሴቶችን ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ለመቅረፍ መንግሥት ቆራጥና ጠንካራ ፖሊሲዎችን እና ህግችን አውጥቶ ለማስፈፀም መንቀሳቀስ አለበት፡፡

የሴቶች እኩል ተሳታፊነት ቀላል የፍትህ እና የዴሞክራሲ ጥያቄ ብቻም አይደለም። እንዲያውም የሴቶች መብት እና ጥያቄዎች በሁሉም መስክ ትኩረት እንዲሰጠው እንደመሰረታዊ ቅድመ-ሁኔታ መታየት አለበት። ከዚህም በተጨማሪ እንደማህበረሰብ እና እንደሀገር በሴቶች ፖለቲካ ውስጥ መሳተፍ የሚያስገኘውን ጥቅም በመረዳት ሴቶችን በተለያዩ መንገዶች ወደፖለቲካ እንዲመጡ ማበረታታት ተገቢ ነው፡፡

ለምሳሌ በተለያዩ የመንግሥት ቢሮዎች፣ በፓርላማ እና በምክርቤቶች ውስጥ የስርዓተ-ፆታ ኮታ ሥርዓትን ማስተዋወቅ አንዱ መሣሪያ ነው፡፡ በርካታ ሀገራትም ይህን አሠራር እየተጠቀሙበት ይገኛሉ፡፡

ነገር ግን ከዚህ በተጨማሪ ትርጉም ያለው እና ዘላቂ መፍትሄን ለማምጣት በማኅበረሰብ ውስጥ የአስተሳሰብ ለውጥን ማስፈን አስፈላጊነቱ የጎላ ነው፡፡ በተለይም ማኅበረሰቡ ለሴት መሪዎች ያለውን አመለካከት እንዲቀይር ሁሉም አካላት በእርብርብ መሥራት ይገባቸዋል፡፡

ሴቶችን ከልጅነት ጀምሮ በማስተማር ብቁ እና ጠንካራ እንዲሆኑ ማድረግ ተገቢ ነው፡ ፡ በቤት ውስጥ ተወስነው እንዳይቀሩ ይልቁንም መሆን የፈለጉትን መሆን የሚችሉበት ሃገር እና ማኅበረሰብ መፍጠርም ያስፈልጋል፡፡

በብዛት ወንዶች በሚሳተፉበት የፖለቲካ ምህዳር ድምፃቸው እንዳይዋጥ እና ተሳትፏቸው ትርጉም አልባ እንዳይሆን የተለያዩ የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎችን ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ሊያገኙ ይገባል፡፡ የፖለቲካ ፓርቲዎችም ከመራጩ ሕዝብ ግማሹን የሚይዙት ሴቶችን ያላማከለ የፖለቲካ ሥርዓት እንደማያዋጣ በመረዳት፣ ሴቶች በአመራርነት ቁልፍ ቦታዎችን እንዲይዙ ማበረታታት አስፈላጊም ሲሆን ሳቢ አሰራሮችን (incentives) መቀየስ እና እጩ በሚያቀርቡበት ጊዜም ጾታ ተመጣጣኝ አቀራረብ እንዲሆን መሥራት ይኖርባቸዋል፡፡ በተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች በመንግሥት እና ሌሎች የአመራር ኃላፊነት ላይ ያሉ ሴቶችም እርስ በእርሳቸው መደጋገፍ እና ልምድ መለዋወጥ እንዲሁም ሌሎችን ማበረታታት ይኖርባቸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ያለሴቶች ውክልና እና ንቁ ተሳትፎ የምናልማትን ታላቅ ዴሞክራሲያዊት ሀገር መሥራት ቀርቶ ልናጣው የማይገባን ይህ የዴሞክራሲ ሽግግር አንድ እርምጃ ወደፊት መሔድ እንደማይቻለው ይገነዘባል፡፡ ሴቶችን ለማሳተፍም ከየትኛውም ጊዜ በላይ ጠንክሮ እየሠራ ይገኛል፡፡ ሴቶችም ለሀገራቸው እና ለራሳቸው መብቶች ለመቆም ወደኋላ ሳይሉ መንቀሳቀስ እንደሚገባቸው በመረዳት ከፖለቲካዊ እና ዴሞክራሲያዊ ትግሉ ጋር የሴቶችም ትግሎችና ፖለቲካዊ ጥያቄዎችን አብሮ ማስኬድ እንደሚገባው በፅኑ ያምናል፡፡

# የኢዜማ ድጋፍ ማኅበር በዳላስ ተመሠረተ

ጥቅምት 13 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)




ፎቶ ክሬዲት፡- ከማህበራዊ ድህረ ገፅ

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ዓለምአቀፍ ድጋፍ ማኅበር በቴክሳስ ግዛት በዳላስ ከተማ ምርጫ ማካሄዱን የኢዜማ ዓለምአቀፍ አባላት ተጠሪ ኢዮብ መሳፍንት ለዜጎች መድረክ ገለፁ፡፡

ለከተማ ኮሚቴ አመራርነት 5 ሰዎች ሲመረጡ ለክፍለ ዓለማትና ዓለምአቀፍ ኮሚቴዎች አመራርነት ሶስት ሰዎች መመረጣቸውን ለዜጎች መድረክ የደረሰው መረጃ ያስረዳል፡፡ የዓለምአቀፍ ድጋፍ ማኅበር ምርጫዎች በተለያዩ ከተሞች እየተካሄደ እንደሚቀጥል ተጠሪው ጠቁመዋል፡፡

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ዓለምአቀፍ ድጋፍ ማኅበር በሰሜን አሜሪካ በተለያዩ ከተሞች ምርጫዎችን እንዳካሄደ የሚታወስ ነው፡፡

# ሴቶች ለማኅበራዊ ፍትህ በሚል ርዕስ የፓናል ውይይት ይካሄዳል

ጥቅምት 13 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) የሴቶች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ የፊታችን ቅዳሜ ጥቅምት 15 ቀን 2012 ዓ.ም ሴቶች ለማኅበራዊ ፍትሕ በሚል ርዕስ በሰሜን ሆቴል የፓናል ውይይት እንደሚያካሄድ የኢዜማ ሴቶች ጉዳይ ተጠሪ ከውሰር እድሪስ ለዜጎች መድረክ ገለፁ፡፡

ውይይቱ በኢዜማ መሪ ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር) መክፈቻ ንግግር የሚጀመር ሲሆን በውይይቱ ላይ ማኅበራዊ ፍትህን በሚመለከት ከውሰር እድሪስ የመወያያ ሀሳብ የሚያቀርቡ ሲሆን የስርአተ ጾታ ባለሙያ የሆኑት ስኂን ተፈራ (ዶክተር) የፆታ እኩልነትን በሚመለከት የመወያያ ሀሳብ የሚያቀርቡ ይሆናል፡፡

የፆታ ጉዳይ ከማኅበራዊ ፍትህ ጋር የሚያያዝ መሆኑን ያነሱት ተጠሪዋ፣ ኢዜማ ማኅበራዊ ፍትህን የፖለቲካ ፍልስፍናው አድርጎ ከመከተሉ አንፃር ማኅበራዊ ፍትሕን በማስፈን ረገድ ሴቶች ምን ዓይነት ሚና ይኖራቸዋል የሚለውን ማመላከት የፓናል ውይይቱ ዓላማ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ውይይቱ የፊታችን ቅዳሜ ጥቅምት 15 ቀን 2012 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ጀምሮ በሰሜን ሆቴል ይካሄዳል፡፡